አፍሪካ ቲቪ

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

4

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት “የልብ ተግባራት”

3

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ተውባ (ወደ አሏህ መመለስ)

- **ተውባህ** (ንስሃ መግባት) ሁልጊዜም ግዴታ ነው፡፡
- በስህተቶች ላይ መውደቅ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ነው፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹የአደም ልጅ ሁሉ ተሳሳች ነው (ሐጢዓቱ ብዙ ነው) ከተሳሳቾች ሁሉ የበለጠ ደግሞ ተውባ አድራጊዎች (ንስሃ ገቢዎች) ናቸው›› ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ባትወነጅሉ (ኋጢዓት ባትሰሩ) ኖሮ እናንተን አጥፍቶ ሊሎች እያጠፉ ከዚያ የአላህን ምህረት እየጠየቁ የሚምራቸው ሕዝቦች ይፈጥር ነበር›› ብለዋል፡፡

- ተውባን ማዘግየትና በወንጀል ላይ መቆየት ወንጀል ነው፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

- ሼይጣን የሰውን ልጅ ከሰባት እንቅፋቶች (መሰናክሎች) በአንዱ ማደናቀፍ ይፈልጋል፡፡
- በአንዱ ሲያቅተው ወደ ሌላው ይተላለፋል፡፡

1) የሺርክ እና የኩፍር (የክህደት) እንቅፋት፤

2) ይህ ካልተሳካ በእምነቱ ውስጥ ያልሆነ ነገር በማስገባትና ነብዩን ﷺ እና ባልደረቦቻቸውን መንገድ እንዳይከተል በማድረግ (ቢድዓ ላይ ለመጣል ይጥራል)፤

- ሼይጣን የሰውን ልጅ ከሰባት እንቅፋቶች (መሰናክሎች) በአንዱ ማደናቀፍ ይፈልጋል፡፡ ...

3) ይህን ካልቻለ ታላላቅ ወንጀሎች በማሰራት፤

4) ይህን ካልሆነለት ትናንሽ ወንጀሎችን በማሰራት፤

5) ይህን ካልቻለ የተፈቀዱ (ሙባህ) ነገሮችን በማስበዛት፤

- ሼይጣን የሰውን ልጅ ከሰባት እንቅፋቶች (መሰናክሎች) በአንዱ ማደናቀፍ ይፈልጋል፡፡ ...

6) በዚህ ካልተሳካለት በላጭ ነገሮችን በማስተው ዝቅተኛ አጅር ያላቸውን በማሰራት (አጅሩ ከፍ ያለውን በማስተው)፤

7) በዚህ ካልተሳካለት የሰውንም ሆነ የሼይጣንን ጂኖች (ጋኒኖች) በሱ ላይ በማሰማራት ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- **ወንጀሎች ብዙ አይነቶች ናቸው፡፡**

1. ታላላቅ ወንጀሎች ሲሆኑ እነሱም ዱንያዊ ቅጣት ለምሳሌ ግርፋት ግድያ ወይም በአኺራ እንደሚያስቀጣ ዛቻ፤ ቁጣ እርግማን ወይም እምነት የለውም የተባለበት ጉዳይ ነው፡፡

2. ትናንሽ ወንጀሎች ሲሆን እነሱም በአንደኛው ከተጠቀሱት በታች የሆኑት ናቸው፡፡

- እዚህ ላይ ትናንሽ ወንጀሎችን ወደ ከፍተኛው ወንጀሎች የሚያደርሱ ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡
- ዋና ዋናዎቹ በጥቃቅን ወንጀሎች ላይ መዘውተር፤ እነሱን መደጋገም እነሱን አቃሎ ማየት በወንጀሉ መኩራራት ወይም ወንጀሉን ግልፅ አድርጎ በይፋ በአደባባይ መስራት ነው፡፡
- ከሁሉም ወንጀሎች ተውባ ማድረግ ይቻላል፡፡
- ፀሀይ በመግቢዋ እስካልወጣች ወይም ከተውበተኛው ሩህ ጣረሞት ላይ እስካልሆነች ድረስ ተውባ ማድረግ ይቻላል፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

- አንድ ሰው ተውባ ሲያደርግ ምን ያገኛል፡-
- የትክክለኛ ተውበት (ለአሏህ የተደረገ ተውባ) ባለቤት ምንዳው ወንጀሉ (ኋጢዓቱ) ከብዛቱ አንፃር ሰማይ ቢደርስ እንኳን ሥራው ወደ መልካም ነገር ይለወጥለታል፡፡
- ከሁሉም ወንጀሎች ተውባ ማድረግ የሚፈለግና የተፈቀደ ነው፡፡

- ተውባ ተቀባይነት እንዲኖረው ወሣኝ መስፈርቶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

1) ወንጀልን መተው

2) ባለፈው ነገር መፀፀት

3) ወደፊት ላለመመለስ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ ሲሆን

4) ወንጀሉ ከፍጡር ጋር የተያያዘ ከሆነ ደግሞ
የሰዎችን ንብረት መመለስ ግድ ይላል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ሰዎች ወደ አላህ ንስሃ ከመግባት አኳያ አራት አይነት ናቸው፡፡
- 1) እስከመጨረሻ ድረስ ጻንቶ የሚቀጥልና ሰዎች ሊጠነቀቁት ከማይችሉት ጥቃቅን ስህተቶች በስተቀር ወደ ነበረበትም ሆነ ወደ ሌላ ወንጀል የማይመለስ ነው፡፡ ይህ ተግባር ኢስቲቃማ ይባላል፡፡
- ይህን የፈፀመ ሰውም ትክክለኛ ተውባ ያደረገ (ንስሃ የገባ) ይባላል፡፡

  ይህ አይነት አቋም ያላት ነፍስ የተረጋጋች ነፍስ ትባላለች፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

## 2) መሰረታዊ የአምልኮ (ዋና ዋና ኢባዳዎችን) ተግባሮችን እየፈፀመ ሆን ብሎ ሳይሆን በልዩ ልዩ ወንጀሎች ይዘፈቃል፡፡

- ሆኖም በተሳሳተ ቁጥር እራሱን ይወቅሳል ድጋሜ ላለመስራትም ይወስናል፡፡
- ይህ አይነት አቋም ያላት ነፍስ ራሷን ወቃሽ ትባላለች፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

3) የተወሰነ ጊዜ ቆብቶ እና ቀጥ ብሎ ከጊዜ በኃላ በአንዳንድ ላይ ይወድቃል። በጥቂት ወንጀሎች ላይ ቢጠቃም ብዙ ወንጀሎችን ተቋቁሞ ያልፋል። ወንጀሎችንም እንደፈፀመ ይፀፀታል ወደፊት ላለመመለስ ቃል ይገባል። ይህ አይነቱ ሰው በማዘግየቱና ነገ ዛሬ በማለቱ መጨረሻው አደጋ ነው። ምክንያቱም ሳይቆብት ሊሞት ይችላልና ነው። የተግባሮች ምንነት የሚወሰነው ከመጨረሻው አኳያ ነውና ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

4) የተወሰነ እድሜውን ቆብቶ ከዚያ በኃላ በልዩ ልዩ ወንጀሎች ውስጥ የሚዘፈቅ ነው፡፡

- ከዚያም በስህተቱ የማይፀፀትና በጥፋቱ የማያምን ነው፡፡
- ይህ አይነት ነፍስ ያለው ሰው ባለመጥፎ ነፍስ ይባላል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com